የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

7 ኛ ዓመትቁጥር 18 ሠመራ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	7th Year No. 18 Samara 7th, 2002

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ----------

ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 18/1994 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልል ራሱን የቻለ የክልል መንግስት ሆኖ በህገ መንግስት መቋቋሙ የሚታወቅ ሲሆን ክልሉን ብሔራዊ ክልል ከሚያሰኙት መለኪያዎች አንዱ የራሱ ቋንቋ መናገሩ ነው።የአፋር ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲወጣ በጽሑፍ ቋንቋነቱ ዳብሮ መገኘት አለበት። ይህንን ብሔራዊና አጣዳፊ ጉዳይን ከግቡ ለማድረስ እንዲቻል አንድ የተሟላ የአፋርኛ ቋንቋ የጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ማቋቋም አስፈልጓል።

በመሆኑም በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 18/1994 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

1. «ክልል» ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው፣
2. «ቦርድ» ማለት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ቦርድ ማለት ነው፣
3. «ማዕከል» ማለት የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ማለት ነው፣

ክፍል ሁለት

አንቀጽ 3

የማዕከሉ መቋቋም

1. የአፋር ቋንቋ ጥናትና ማበልፀጊያ ማዕከል ከዚህ በኋላ ማዕከሉ እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

አንቀጽ 4

የማዕከሉ ተጠሪነት

የማዕከሉ ተጠሪነት ለቦርድና ለክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል፣

አንቀጽ 5

የማዕከሉ ዋና ጽ/ቤት

የማዕከሉ ዋና ጽ/ቤት በሰመራ ሆኖ እንደየአስፈላጊቱ በየዞኖችና በወረዳዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

አንቀጽ 6

ዓላማ

ማዕከሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1. የአፋር ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ማሳደግና ማስፋፋት፣
2. በአፋርኛ ቋንቋ ባዕድ የሆኑ ቃላቶች፣ ፅንሰ ሐሳቦችና ተርሚኖሎጂስ በአንድ ወጥነት መጠቀም የሚያስችል ምቹ መንገድን ይፈጥራል፣
3. ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ጋር በመተባበር የክልሉ ሕብረተሰብ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመማር መብቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል። የመጀመሪያ ሳይክል የትምህርት መሳሕፍት ዝግጅት ላይ የበኩሉን ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ ይወጣል፣
4. ከክልሉ መንግስት መስተዳድር አካላት በሚያገኘው ድጋፍ በመታገዝ ቋንቋን የማስተማር ሂደት እንዲፋጠን ያደርጋል፣
5. ልዩ ልዩ ኘሮግራሞችን በመንደፍ የክልሉ ነዋሪ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋውን እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያስተምራል፣
6. የአፋር ቋንቋን ሥረ መሠረት ምርምርና ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ያሰባስባል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣

7. በክልሉ መንግስት የሚወጡ ልዩ ልዩ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ወደ አፋርኛ ቋንቋ እንዲተረጐም ጥያቄ ሲቀርብለት የትርጉም ሥራዎችን ያከናውናል፣

አንቀጽ 7

የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር

1. የማዕከሉ የአፋር ቋንቋ እንዲበለጽግ ልዩ ልዩ የአግግፍ ስልቶችን ይነድፋል፣ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ጥረት ያደርጋል፣
2. የየአካባቢ አነጋገሮችና አባባሎች መሠረታቸውን ሳይስቱ ለተሻለ ግልጋሎት እንዲውሉ ያደርጋል፣
3. አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች የሚወከሉና የቴክኖሎጂ ቃላትን የሚተረጉሙ አዳዲስ ቃላትን መፍጠርና ማሰራጨት የመሳሰሉትን ይሠራል፣
4. ድምጾችን በሚወክሉና በሆሄዎች ላይ የሚጨመሩና የሚቀነሱ ምልክቶችን በጥናት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
5. የአፋር መዝገበ ቃላትን ያዘጋጃል፣አሳትሞ ያሠራጫል፣
6. ልዩ ልዩ የቋንቋና የታሪክ መጽሐፍትን ያሰባስባል፣
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአንደኛ ደረጃን የጐልማሶች ትምህርት መማሪያ ካሪክለም ያዘጋጃል፣
8. ልዩ ልዩ የቋንቋ ኮርሶችን ያዘጋጃል ያስተምራል፣
9. የአፋርኛ ቋንቋና የታሪክ ጥናት ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፣
10. በሥራ ለሚገኙ ባለሙያዎች ለጥናትና መርምር ሥራው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የስልጠና እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፣
11. ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች ወደ አፋርኛ እንዲሁም በተቃራኒው ከአፋርኛ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች የትምህርትና ሌሎች መጽሐፍት የትርጉም ሥራዎች ያከናውናል፣
12. በክልሉ መንግስት የሚወጡ ህጎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወደ አፋርኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ ጥያቄ ሲቀርብ የትርጉም ሥራዎችን ያከናውናል፣
13. ለቋንቋው እድገት አስተዋጽኦ በጽሑፍም ሆነ በቃል የሚያበረክቱ ወገኖችን ያበረታታል ይሸልማል፣

ክፍል ሶስት

የቦርዱ አቋም

አንቀጽ 8

የቦርድ አባላት

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ቢሮዎች የሚወክሉና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል።

አንቀጽ 9

የቦርዱ ተጠሪነት

የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

አንቀጽ 10

የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ የተዘረዘሩት የማዕከሉ ዓላማዎችን ያስፈጽማል፣
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ የተዘረዘሩትን የማዕከሉን ስልጣንና ተግባር በበላይነት ይመራል፣ የአዋጁን አፈፃፀም በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
3. የማዕከሉ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን ውስጠ ደንብ (መመሪያ) ያፀድቃል፣
4. እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ አባላትንም ይመርጣል፣
5. የዓመቱን በጀትና የሥራ እቅድ ያፀድቃል፣
6. በሌሎች አስፈላጊ በሆኑ የማዕከሉ ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል፣

አንቀጽ 11

የቦርዱ ስብሰባ

1. የቦርዱ ስብሰባ በየ 6 ወሩ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ በማንኛውም ጊዜ ሊደረግ ይችላል፣
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ በግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ አባላት ውሳኔ በስብሰባው ከተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲያገኙ ሆኖ ድምሩ አከኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወገን ድምጽይኖረዋል።

አንቀጽ 12

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

1. ሥራ አስኪያጁ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣
2. ለማዕከሉ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ፣

ሀ/ የማዕከሉን እቅድና የፋይናንስ አጠቃቀም ይቆጣጠራል ይከታተላል፣

ለ/ ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሐ/ የማዕከሉን የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶና አጠናክሮ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በፀደቀው መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

መ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፣

ሠ/ የማዕከሉን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አጠናክሮ ለቦርድ ያቀርባል፣

ረ/ የጥናት፣ የስብሰባና የመሳሰሉ ከፍተኛ ወጭዎች ላይ ይወስናል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 14

የበጀት ምንጭ

የክልሉ መንግስት የሚመድበውና ከሌሎች የሚገኝ ድጋፍ ይሆናል።

አንቀጽ 15

ስለሂሳብ መዛግብት

1. ማዕከሉ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት በሚታቀፍበት ቹል ውስጥ ይኖሩታል፣
2. የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብቶችና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ቀርበው በየዓመቱ ይመረመራል።

አንቀጽ 16

ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ማንኛውም ሌላ ሕግ ከዚህ አዋጅ ጋር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወጡ ሕጎች ጋር የሚቃረኑ ከሆነ በአዋጁ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

አንቀጽ 17

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሰኔ 30 1994 ዓ.ም

ሠመራ

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር